የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 73
ADDIS ABABA 25th July, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የእቃዎች ሽያጭ ውሎች ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……ገጽ ፲፪ሺ፯፻፳፪

## Content

Proclamation No.1220/2020

United Nations Convention on Contracts for the International Sale of Goods Ratification Proclamation............................................Page 12,722

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

**ስለዓለም አቀፍ የእቃዎች የሽያጭ ውሎች የወጣውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ዓለም አቀፍ የእቃዎች የሽያጭ ውሎች ስምምነት ሚያዚያ ፫ ቀን ፩ሺ፱፻፸፪ ዓ.ም የወጣ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማፅደቅ ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች በእቃዎች ዓለም አቀፍ ሽያጭ ውሎች ግንኙነት ውስጥ ያላቸውን ተቀባይነት ከፍ የሚያደርግ ስለሚሆን፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የእቃዎች ሽያጭ ውሎች ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፳/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1220/2020

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE UNITED NATIONS CONVENTION ON CONTRACTS FOR THE INTERNATIONAL SALE OF GOODS**

**WHEREAS**, the United Nations Convention on Contracts for the International sale of goods was adopted on 11th April 1980;

**WHEREAS**, ratifying the Convention enhances domestic traders' engagement in contracts for the international sale of goods;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 25th day of June, 2020;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "United Nations Convention on Contracts for the International Sale of Goods Ratification Proclamation No.1220/2020"

**፪. ተዓቅቦ**

፩/ በስምምነቱ አንቀጽ ፺፭ መሰረት፣ የስምምነቱ አንቀጽ ፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስትን አይገዛውም፡፡

፪/ የተዋዋዩ ወገን የንግድ ስራ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝበት ጊዜ የሽያጭ ውል ወይም ማሻሻያው ወይም ማቋረጫው ወይም የውል አቀራረብ ወይም አቀባበል ወይም የሀሳብ ማሳያ በጽሁፍ ሳይሆን በማንኛውም ዓይነት ፎርም ሊደረግ እንደሚችል የሚደነግገው የስምምነቱ አንቀጽ ፲፩፣ ፳፱ ወይም ክፍል ሁለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ላይ በስምምነቱ አንቀጽ ፺፮ መሰረት ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

**፫. የስምምነቱ መጽደቅ**

የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የእቃዎች ሽያጭ ውሎች ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፬. የንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ኃላፊነት**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና እንዱስትሪ ሚኒስቴር ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፭. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፳፻፲፪ ዓ.ም**

**ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**2. Reservation**

1/ In accordance with Article 95 of the United Nations Convention on Contracts for the International Sale of Goods, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia will not be bound by Sub-Article (1) (paragraph b) of Article 1 of the Convention.

2/ In accordance with Article 96 of the Convention, any provision of Article 11, Article 29, or Part II of the Convention that allows a contract of sale or its modification or termination by Agreement or any offer, acceptance, or other indication of intention to be made in any form other than in writing, does not apply where any party has his place of business in the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

**3. Ratification of the Convention**

The United Nations Convention on Contracts for the International Sale of Goods is hereby ratified.

**4. Responsibility of the Ministry of Trade and Industry**

The Ministry of Trade and Industry of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to follow up the implementation of the Convention in collaboration with other government organs.

**5. Effective Date**

This Proclamation shall come into force up on publication in the *Federal Negarit Gazette.*

**Done at Addis Ababa, on this 25th day of July, 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**